# በጉምሩክ ሥራ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በአስተዳደራዊ ውሣኔ ለመጨረስ የወጣ መመሪያ


የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

ሚያዝያ 2001 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

## *በጉምሩክ ሥራ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በአስተዳደራዊ ውሣኔ ለመጨረስ የወጣ መመሪያ ቁጥር 12/2001*

በጉምሩክ ሥራ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን ባህሪና በሕዝብና በመንግስት ጥቅም ላይ የሚያደርሱትን ጉዳት ከግምት ውስጥ በማስገባት በአስተዳደራዊ ውሣኔ እልባት እንዲያገኙ ለማድረግ እንዲቻል ግልጽና ወጥ የሆነ የአሰራር ስርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፣

በአስተዳደራዊ ውሣኔ የሚሰጥባቸውን የጉምሩክ ወንጀሎች ዓይነት፣ የሚወሰዱ የቅጣት እርምጃዎችና የውሣኔ አሰጣጥ ስነ ስርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፣

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 107 (2) በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "በጉምሩክ ሥራ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በአስተዳደራዊ ውሣኔ ለመጨረስ የወጣ መመሪያ ቁጥር 12/2001" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሲባል፡-

1) "የጉምሩክ ወንጀሎች" ማለት

ሀ/ ወደ አገር ለሚገባ እቃ የቀረበው መግለጫ /ዲክላራሲዮን/ እና/ወይም ደጋፊ ሰነዶች ላይ በተገለፀውና በእቃው ላይ በተደረገ የፍተሻ ውጤት መካከል የሚገኝ የብዛት፣ የስሪት አገር፣ የምርት ዘመን፣ የመጠን፣ የአገላለጽ ወይም

ሌላ በቀረጥና ታክስ ላይ ልዩነት የሚያስከትል ማንኛውም ዓይነት ድርጊት መፈፀም ነው፡፡

ለ/ ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ /ፍራንኮቫሉታ/ በቀረጥና ታክስ ክፍያም ሆነ ከቀረጥና ታክስ ነፃ ወደ አገር ለማስገባት በሕግ ከተፈቀዱት እቃዎች መጠን በላይ ወይም ውጪ ይዞ መገኘት፡፡

ሐ/ በሕግ ከማናቸውም ቀረጥና ታክስ ነፃ ሆኖ ወደ አገር የገባን ተሽከርካሪ ወይም ሌላ እቃ ከባለመብቱ ወይም በሕግ ከተፈቀደላቸው ሰዎች ውጪ በሌሎች ይዞታ ስር ማድረግ ነው፡፡

2) "ልዩነት" ማለት በተፈፀመው የጉምሩክ ወንጀል ለተያዘው እቃ ሊከፈል የሚገባው ቀረጥና ታክስ ከብር500,000 ያልበለጠ እና በልዩነት የተገኘው ቀረጥና ታክስ ቀደም ሲል ከተከፈለው ቀረጥና ታክስ ከ25% ያልበለጠ ሲሆን፣ ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ ወደ አገር እንዲገባ ከተፈቀደው መጠን በላይ ወይም ውጪ የመጣን እቃና መብቱ የሌለው ሰው ሲገለገልበት የተያዘ የቀረጥ ነፃ እቃን ይጨምራል፡፡

3) "አቤቱታ አጣሪ ቡድን" ማለት በባለስልጣኑ የሚቋቋም የቅሬታ ሰሚ አካል ነው፡፡

4) "ዲክላራሲዮን" ማለት በአዋጅ ቁጥር 622/2001 የተሰጠውን ትርጓሜ ይይዛል፡፡

5) "አዋጅ" ማለት የጉምሩክ አዋጅ 622/2001 ነው፡፡

6) "ባለሥልጣን" ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ነው፡፡

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በአንቀጽ 2/1 ላይ በተዘረዘሩት የጉምሩክ ወንጀሎች ላይ ብቻ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 4. በመመሪያው የማይሸፈኑ ወንጀሎች

1) ይህ መመሪያ

ሀ/ በሕግ ክልከላ እና ገደብ በተደረገባቸው እቃዎች፣

ለ/ በኮንትሮባንድ እቃዎች፣

ሐ/ በልዩነት የተገኘው ቀረጥና ታክስ ቀደም ሲል ከተከፈለው ቀረጥና ታክስ ከ25% የበለጠ እና

መ/ በልዩነት የተገኘው ቀረጥና ታክስ ከብር 500,000 የበለጠ ልዩነት በተገኘባቸው፣

ሠ/ በወጪ እቃዎች

ረ/ ለአራተኛ እና ከዚያ በላይ የጥፋት ሪከርድ በተያዘባቸው ላይ

ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ላይ በተዘረዘሩት እቃዎች ላይ ወንጀል ተፈጽሞ ሲገኝ በልዩነት የተገኙት እና ዲክላራሲዮን የቀረበባቸው እቃዎች በሙሉ ተይዘው ምርመራ እንዲጣራባቸው ይደረጋል፡፡

## ክፍል ሁለት

## በአስተዳደራዊ ውሣኔ ስለመጨረስ

### 5. መሠረቱ

ባለሥልጣኑ፡-

1. የጉምሩክ ስነ ስርዓት አሟልቶ ወደ አገር በገባው እቃ ላይ የተገኘው ልዩነት ሊከፈል ከሚገባው የቀረጥና ታክስ መጠን ከ25% እና ከብር 500,000 ያልበለጠ ከሆነ፣ ወይም
2. ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ በቀረጥና ታክስ ክፍያም ሆነ ከቀረጥና ታክስ ነፃ ወደ አገር ለማስገባት በሕግ ከተፈቀዱት እቃዎች መጠን በላይ ወይም ውጪ የተገኘው የቀረጥና ታክስ መጠን ከብር 20,000 ያልበለጠ ከሆነ፣ ወይም
3. ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆኖ ወደ አገር የገባን እቃ ከባለመብቱ ወይም በሕግ ከተፈቀደላቸው ሰዎች ውጪ ሌሎች ሲገለገሉበት የተገኘ እና ሊከፈል የሚገባው ቀረጥና ታክስ ከብር 500,000 ያልበለጠ እንደሆነ፣

በዚህ መመሪያ መሠረት ጉዳዩን በአስተዳደራዊ ውሣኔ ለመጨረስ ይችላል፡፡

### 6. ስለ ውሣኔ አሰጣጥ እና ማሳወቅ

የጉምሩክ ስነ ስርዓት መተላለፍ አጣሪና ውሣኔ ሰጪ ቡድን ልዩነት የተገኘበት ዲክላራሲዮን ወይም ሰነድ በደረሰው በ5 ቀናት ውስጥ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 እና

10 መሠረት የቅጣቱን ልክ ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ቅጽ መሠረት ለእቃው ባለቤት፣ ወኪል ወይም ለጉምሩክ ስነ ስርዓት አስፈፃሚው ያሳውቃል፡፡

## 7. ማመልከቻ ስለማቅረብ

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 የተደነገገው ቢኖርም ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆኖ ወደ አገር በገባ እቃ ላይ የተፈፀመ የጉምሩክ ወንጀል በአስተዳደራዊ ውሣኔ የሚያልቀው የእቃው ባለቤት፣ ወኪል ወይም ተጠቃሚ ለሕግ ማስከበር የሥራ ሂደት ማመልከቻ ያቀረበ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡

## 8. ማመልከቻን ስለመመርመር

1) የሕግ ማስከበር የሥራ ሂደት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 መሠረት ማመልከቻ የቀረበለት እንደሆነ በ5 የሥራ ቀናት ጉዳዩን መርምሮ መዝገቡን ለዐቃቤ ሕግ ያስተላልፋል፡፡
2) የዐቃቤ ሕግ የሥራ ሂደት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የቀረበለትን የምርመራ መዝገብ መርምሮ በ3 የሥራ ቀናት ውስጥ በመመሪያው አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የሚከፈለውን ቅጣት እና የተያዘው እቃ እንዲለቀቅ በመወሰን መዝገቡን ለሕግ ማስከበር የሥራ ሂደት ይመልሳል፡፡
3) የሕግ ማስከበር የሥራ ሂደት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የተላለፈውን ውሣኔ ለጉምሩክ ስነ ስርዓት አፈፃፀም የሥራ ሂደት በሁለት የሥራ ቀናት ያስተላልፋል፡፡

# ክፍል ሶስት

# ስለ ቅጣት

## 9. የቅጣት ልክ

1) በተፈፀመው የጉምሩክ ወንጀል የተገኘው ልዩነት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ስር የሚወድቅ ከሆነ በልዩነት የተገኘው ቀረጥና ታክስ መከፈሉ እንደተጠበቀ ሆኖ የልዩነቱን እጥፍ በማስከፈል እቃው ይለቀቃል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ላይ የተገለፀው ቢኖርም ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆኖ ከገባ እቃ ጋር በተያያዘ ለተፈፀመ የጉምሩክ ወንጀል እቃው ወደ አገር በገባበት ጊዜ ለእቃው የሚከፈለው ቀረጥና ታክስ እንደተጠበቀ ሆኖ የቀረጥና ታክሱን 25% መቀጫ እንዲከፈል ተደርጐ እቃው ይለቀቃል፡፡

## 10. በተደጋጋሚ ጥፋቶች ላይ ስለሚሰጥ ውሣኔ

1) ጥፋቱ ለሁለተኛ ጊዜ ተፈጽሞ የተገኘ እንደሆነ በልዩነት የተገኘው እቃ ላይ ቀረጥና ታክስ መከፈሉ እንደተጠበቀ ሆኖ የልዩነቱን ሁለት እጥፍ በማስከፈል እቃው ይለቀቃል፡፡
2) ጥፋቱ ለሶስተኛ ጊዜ ተፈጽሞ ከተገኘ በልዩነት የተገኘው እቃ ላይ የሚከፈለው ቀረጥና ታክስ መከፈሉ እንደተጠበቀ ሆኖ የልዩነቱን ሶስት እጥፍ በማስከፈል እቃው ይለቀቃል፡፡
3) ጥፋቱ ለአራተኛ ጊዜና ከዚያ በላይ ከሆነ ጉዳዩ በሕግ እንዲታይ ይደረጋል፡፡
4) ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሲባል ተደጋጋሚ ጥፋት የሚቆጠረው ይህ መመሪያ ሥራ ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ የተፈፀመ ጥፋት ከሆነ ነው፡፡

# ክፍል አራት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 11. ቅሬታ ስለማቅረብ

1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 እና 10 መሠረት በተሰጠው ውሣኔ ቅሬታ ያለው ሰው ከጉምሩክ ስነ ስርዓት መተላለፍ አጣሪና ውሣኔ ሰጪ ቡድን ውሣኔው በደረሰው በ15 ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለአቤቱታ አጣሪ ቡድን ማቅረብ ይችላል፡፡
2) የእቃው ባለቤት ወይም ወኪል የአቤቱታ አጣሪ ቡድን ውሣኔ በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ካላቀረበ ወይም ጉባኤው በወሰነው ውሣኔ መሠረት ለመፈፀም ፈቃደኛ ካልሆነ በልዩነት የሚፈለግበትን ቀረጥና ታክስ እና ቅጣቱን ለመሸፈን በሚችልበት መጠን በስሙ ተመዝግቦ

የሚገኝን እቃ እንዲሁም አስቀድሞ የተከፈለው ቀረጥና ታክስ ውርስ ይደረጋል፡፡

## 12. ልዩነት ስለመመዝገብ

ወደ አገር በገቡ እቃዎች ላይ የተገኘን ልዩነት በዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች መሠረት እልባት የሚሰጥ ማናቸውም የባለስልጣኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሁሉም የባለስልጣኑ ጽ/ቤቶች መረጃውን ሊያገኙ በሚችሉበት ሁኔታ በአሲኩዳ የመረጃ መረብ በተመዘገቡበት ዲክላራሲዮን ላይ በጥንቃቄ የመመዝገብ ግዴታ አለበት፡፡

## 13. ሪፖርት ስለማቅረብ

የጉምሩክ ስነ ስርዓት መተላለፍ አጣሪና ውሣኔ ሰጪ ቡድንና የሕግ ማስከበር የሥራ ሂደት በዚህ መመሪያ መሰረት ውሣኔ የተሰጣቸውን ጉዳዮች መዝገብ ያደራጃሉ፣ በየወሩም ለመረጃ ምርመራና ስጋት ስራ አመራር ሪፖርት ያቀርባሉ፡፡

## 14. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

1) ይህ መመሪያ ከመጽናቱ በፊት በእንጥልጥል ላይ ያሉና በመመሪያው ሊታዩ የሚችሉ ጉዳዮች በዚህ መመሪያ መሠረት ውሣኔ ሊያገኙ ይችላሉ፡፡
2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ ድንጋጌ በፍርድ ቤት እየታዩ ያሉትን የወንጀል ጉዳዮች አይመለከትም፡፡

## 15. የተሻሩ መመሪያዎች

የጉምሩክ ደንብ መተላለፎችን በአስተዳደራዊ ውሣኔ ለመጨረስ የወጡት መመሪያዎች ቁጥር 37/1998፣ 42/1999 እና 43/1999 በዚህ መመሪያ ተሽረዋል፡፡

16. <u>*መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ*</u>

*ይህ መመሪያ ባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡*

**አዲስ አበባ______________ቀን 2001 ዓ.ም**

**መላኩ ፈንታ**
**የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን**
**ዋና ዳይሬክተር**

## *አስተዳደራዊ ውሣኔ ማሳወቂያ ቅጽ*

♣ **ሁሉም ክፍት ቦታዎች መሞላት አለባቸው**

1. የእቃው ባለቤት ስም ________________________________
2. የጉምሩክ ስነ ስርዓት አስፈፃሚ ስም ________________________________
3. የዲክላራሲዮን ቁጥር ____________________
4. አስቀድሞ የተከፈለው ቀረጥና ታክስ መጠን ብር ________ /_______________/
5. የተገኘው የቀረጥና ታክስ ልዩነት

   5.1 በብር __________ /_______________________/

   5.2 በመቶኛ __________/_______________________/
6. የተፈፀመው የጉምሩክ ወንጀል ዓይነት

   ______________________________________________________________________

   _________________________________________________________
7. የተፈፀመው ጥፋት

   ☐ 1ኛ ጥፋት

   ☐ 2ኛ ጥፋት

   ☐ 3ኛ ጥፋት

   ☐ 4ኛና ከዚህ በላይ

8. የተሰጠ ውሣኔ

   ______________________________________________________________________

   ______________________________________________________________________
9. ሰነዱን የመረመረው ሠራተኛ ስም ________________________

   ፊርማ _____________

   ቀን _______________
10. ያረጋገጠው ኃላፊ ስም ________________________________

    ፊርማ _____________

    ቀን _______________

***ማሳሰቢያ***

1. በዚህ ውሣኔ ቅሬታ ያለው ሰው ውሣኔው በደረሰው በ15 ቀናት ውስጥ ለአቤቱታ አጣሪ ቡድን ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፡፡
2. ቅሬታው በተራ ቁጥር 1 ላይ በተገለፀው ቀናት ውስጥ ካልቀረበ እቃውና ለእቃው አስቀድሞ የተከፈለው ቀረጥና ታክስ ውርስ ይደረጋል፡፡